# <u>ናስተማስለከ፤</u>

ፀጋዬ አበበን በምን እንመስለው፣
ረቢ፣ መምህር፣ ደብተራ ይበቃል ብንለው፤
ወይስ በጠባዩ በበረበር ሆዱ፣
ደግሞስ በጠንካራ በማይዝለው ክንዱ፤
ወይስ በኮስታራ በማይርበው አንጀቱ፣
በመካሪ ቃሉ በአባት ና ቅነቱ?
ፀጋዬ አባይ ናት፣
ለራሷ ደንታ የሌላት::
እሷ ናት አዋሽ፣
ፍጹም የማትዋሽ::
ኦሞ ወንዝ ናት አገር የምታርስ፣
ባሮ ናት በለሳ ጠማማ ግንዳ ግንድ ምትገረስስ፤
ሸበሌ ናት በርከና፣
ለተከፋ ሕዝብ ሰማይ መና፤
እሱን ፍለጋ ከወንድሞቼ ጋር ወጥቼ ከተራራ፣
ትምህርት ቤት ስንቆጥር ስንጣራ፣
አንድ ማእምር አየሁኝ ከዋሸራ፣
በሬ ሳይጠምድ ቅኔ ሲዘራ፤
ቅኔ ሲዘርፍ ሲያበሰጥር፣
ደግሞ ሲቀስም ሲማር፣
አየሁኝ ደብተራውን ጥበብን ሲምስ ሲቆፍር፤
ከዋልድባውያን መነኮሳት ባሕታውያን፣
ከመናንያን ካህናት ሕጋውያን፣
አብሮ ሆኖ በመቋሚያ፣ በከበሮ፣ በጽናጽን፣
አበክረው ሲረግሙ ሳጥናኤልን፤
የያሬድን የ ዋ! ዜማ እየቀዱ፣
ሠራዊተ ዲያብሎስን አረዱ::
እሸት ፀጋዬ ደብተራው ሁሌ እሸት፣
ሰዊት ቅድመ ሰዊት ድኅረ ሰዊት::
ኢትዮጵያ ተረግጣ አንጀቷ ተቦጥቡጦ፣
አጥንቷ ሥጋዋን ዘልቆአል አግጦ፤
ጡቶቿ በዋግምት ተወግመው፣ ጠውልገው ደርቀውም፣
በመኪና ማለቢያ ቢታለብ፣ መጨመቅ አላቆሙም፤
ተሰብቀው ግራና ቀኝ ደረቶቿ ከጀርባዋ፣
ግና ያስተጋባል ድምጿ እንደ መረዋ፤
ዓለም በቃኝ ብላ መንና፣
እርቧት ጠምቷት ተኮሳምና፤
ትጓዛለች ረጅሙን ጉዞዋን፣
ትወጣለች ትወርዳለች አቀበትዋን፤
ወደቀች ሲሏት ትነሣለች፣
ታመመች ሲሏት ትድናለች፤
ውበቷን ዓይተው ሰዊትነቷን፣
ሽፍቶች ከበቧት ሊበልቱ የሠራ አካላቷን፤
ካራቸውን ቢሞርዱ ቢያፋጩትም፣
እየደነዘ ለገመ እንጂ መቁረጥ አልቻለም::

ተናደው አሥረው ገረፏት እንደ ሌባ፣
ሲገርፏት ፀንሳ አደረች አበባ፤
በሁለመናው እሚመስላት፣

በግርማ ሞገስ አስተያየት፥
ተወለደ ፀጋዬ ሰዊት::
እንደ እናቱ የሁሉን ረሀብ ተርቦ፥
በሕልቆ መሳፍርት ፍሞ ተንገብግቦ፤
በርዛታቸው ተንዘፍዝፎ ተንገፍግፎ፥
ለእኛ ለሁላችን ሲል ተጠርቶ ተገርፎ፤
በሕዳጣን ዘቦች ተደፍቶ ተቀጥቅጦ፥
ከትዳሩ ከግል ደስታው ሕዝብን መርጦ፤
ጉርምስናውንና ጉልምስናውን ለሀገሩ ሰጥቶ፥
ሐቅን ወለደ እሷኑ አግብቶ::
እሱ አንድ ሲሆን እልፍ፥
መነመነ ሲሉት እሚገዝፍ፤
እሱ እነ ተስፋዬን ነው፥
ለፋሽስቶች እጅ የማይሰጠው፥
ሽካራ እጁ ፋሽቶችን የለበለበው፥
መቸ ይኸ ብቻ እሱ ነው እነ ግርማቸው፤
እነ ቆንጂት፥ ዮሐንስ ብርሃኔ፥
በውጣ ውረዱ ሊገታ፥
በዕቡይ ሕዳጣን መተብተቧ፥
በምድራዊ ገሞራ መለብለቧ፤
ሕይወቷ በፈይን መጨፈቁ፥
ብርሃን ከአድማሷ መራቁ፤
የሁሌ ዳበሳ ሕላዌዋ፥
የዳዴ የወፌ ቆመች ጉዞዋ፤
እንዲያበቃ እንዲያከትም፥
ፀጋዬ ይታገላል አይታክትም።
ደብተራው አንድ መስሏቸው፥
መሀን ዘረ-ቢስ ብለው፤
ሥር አልባ ሙጃ አርገውት፥
የታሰረ የተሰቃየውን አሰሩት፤
የደማ የቆሰለውን ቀጠቀጡት፥
የተራበ የተጠማውን አስራቡት፤
የታረዘ የተራቆተውን አረዙት፥
የተጠየቀ የጠፋውን ገደሉት፥
የተሰደደ የተንከራተተውን አሳደዱት፥
የማቀቀ የታመመውን አማቀቁት፥
ሐቁ ፀጋዬን ከደይን ወረወሩት፥
ሊያጠወልጉ ሊያከስሙ አስበውት::
አገር በላች ባለቂራ ካራዎች፥
መምህሩን ቀፈደዱት እግር ተወርች፤
የማሆይ ልጅ እሱ፥
ሐቅ ማኅናጸፊያ ልብሱ፤
የገብረ መድኅን የኢሕአፓ ልቃቂት፥
እሷ ራሷ የሀገር ልጅ መድኃኒት፤

መች ለበሽታ እጁን ሰጥቶ፥
የሚኖር ሁሌ አብቦ አሸቶ፤
የጉን ልክፍት ጋኔን ልትረግጡ ልታሹ፥
የመጋኛ የቡዳ መድኃኒት ስትፈልጉ ስታሹ፤
የኢትዮጵያ የገብረ መድኅን ልጅ ጥሩ፥
በአሷ በእማሆይ ልጅ ኩሩ::
ዋኔን ርግብ ፀጋዬን ኰድኩደው፥
አንቺን እናቱን እማሆይን ሰነጣጥቀው፥

የሚተኩሱት የሚገድሉበትን ጠመንጃ አምልከው፤
እነዚያ ልጆችሽን ለቆሪጥ እንደገበሩ፥
እነዚህም በክላሽ ገድለው ከመሩ፤
ፀጋያት አበቦችን ሊያረግፉ፥
ወፍራም ቅርንጫፎችሽን ቀጣጠፉ፥
በሚያስገርም ተአምር ግና አንቺን አገዘፉ፤
ደብተራው ረቢ ናት፥
የሊቃውንት ፍሬ ያረግናት፤
በቃ ከእንግዲህ የለችም አትበሉ፥
ሃሴት አርጉ ምስሎችንም ሳሉ።